# የዲጂታል ማካተት አጠቃላይ የተጠቃሚ ግንዛቤዎች — እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚጠቀሙ የቀድሞ ስደተኞች እና መጤዎች





Te Tari Taiwhenua
Internal Affairs

Te Kāwanatanga o Aotearoa
New Zealand Government

# 1. መግቢያ

ዲጂታል ማካተት ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በማህበረሰብ ውስጥ ለመሳተፍ ሁሉም ሰው እኩል እድል የሚያገኝበት የመጨረሻ-ሁኔታ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል (የዲጂታል ማካተት ጥናት ቡድን፣ 2017)።

ይህ ለቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ መጤዎች የተጠቃሚ ተሞክሮ (UX) ሪፖርት በ Te Tari Taiwhenua ውስጥ ጉዳዮች ክፍል (DIA) ተልዕኮ የተሰጠው የዲጂታል ማካተት የተጠቃሚ ግንዛቤዎች ተከታታይ ሪፖርቶች ክፍል ነው። የተከታታዩ ዓላማ ብዙውን ጊዜ በዲጂታላዊ ተካታች የማይሆኑትን ቡድኖች የኑሮ ተሞክሮ መረዳት ነው።

የቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ መጤዎች ከመንግስት ኢላማ ስነ-ህዝቦች ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት ሌሎች ጋር ሲነፃፀሩ ከመንግስት ተነሳሽነቶችም ዝቅተኛ ድጋፍ ካገኙ ኢላማ ቡድኖች አንዱ ናቸው።

የሪፖርቱን ክፍል 2 ያንብቡ፦ የዲጂታል ማካተት ክምችት፡ ዲጂታል ማካተት በመንግስት ዙሪያ ምን እንደሚመስል።

ጥናቱ ሊያስቀምጥ ያለመው፦

- የቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ መጤዎች ዲጂታል ማካተት ጉዞ ላይ የነበሩ መሰናክሎችን፣ ፈተናዎችን እና የህመም ነጥቦችን መለየት
- ይህ ቡድን በዲጂታል ማካተት ማዕቀፍ ላይ ምን ያህል በዲጂታላዊ የተካተተ እንደሆነ መረዳት።

ጥናቱ በእነዚህ የጊዜ ወቅቶች ውስጥ — በመጀመሪያዎቹ 3 ወራት እና በመጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት ውስጥ የዚህን ቡድን በ ኦቴሮዋ ኒው ዚላንድ ውስጥ የሰፈራ ተሞክሮ ከግምት ውስጥ ያስገባል።

ጥናቱ የተካሄደው ከ ኤፕሪል እስከ ጁን 2021 በ ኒው ዚላንድ ውስጥ በሚገኙ 6 የተለያዩ ቦታዎች ነው። በአጠቃላይ፣ 20 ብሄረሰቦችን የሚወክሉ 41 ተሳታፊዎች ነበሩ። ከተሳታፊዎች ጋር የተደረጉ ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች በአንድ ለአንድ እና ፊት ለፊት መልኩ ነበሩ። አስፈላጊ ሲሆን በቦታው ላይ በሚገኝ ሰው እና በስልክ የአስተርጓሚ እርዳታ ነበር።

## እውቅና

DIA በዚህ UX የጥናት ፕሮጀክት ላይ ታሪካቻውን ላጋሩ እና ለተሳተፉ ሁሉ ሞቅ ያለ ምስጋናውን ይልካል። የዲጂታል ማካተት ቡድኑም እንዲሁ ቃለ-መጠይቆቹን ለማዘጋጀት እና መመሪያ እና አስተያየቶችን ለማቅረብ ከመንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት (NGOs) ማህበረሰቦች ጋር ጭምር ተሳትፎ ለማድረግ ከጥናት አድራጊው ጋር አብሮ በመስራቱ ለብሄር ማህበረሰቦች ሚኒስትር እውቅና መስጠት ይፈልጋል።

በዚህ ሪፖርት ላይ የተመለከቱት መረጃዎች እና ግኝቶች ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸውን ግለሰቦች እና የሚወክሉዋቸውን የተለያዩ ቡድኖች እይታ የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን **DIA** ማስታወስ ይፈልጋል።

## የሪፖርት መረጃ

ለ Te Tari Taiwhenua ውስጥ ጉዳዮች ክፍል እና ለብሄር ማህበረሰቦች ሚኒስትር የተዘጋጀ።

በ Jas Hua የተዘጋጀ።

ቀን፡ ኖቬምበር 30፣ 2021

### ዋቢ

Hua, J. (2021, ኖቬምበር). 'የዲጂታል ማካተት አጠቃላይ የተጠቃሚ ግንዛቤዎች — እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚጠቀሙ የቀድሞ ስደተኞች እና መጤዎች'. ከእንግሊዘኛው ሪፖርት የተተረጎመ 'Summary of Digital inclusion user insights — Former refugees and migrants with English as a second language.' Department of Internal Affairs. https://www.digital.govt.nz/dmsdocument/195~summary-of-digital-inclusion-user-insights-former-refugees-and-migrants-with-english-as-a-second-language/html



# 2. ቁልፍ ግኝቶች

ይህ ክፍል ከስነ-ፅሁፍ ግምገማው እና ከተካሄደው ጥናት፣ እንዲሁም የቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ መጤዎች ዲጂታል ማካተት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሌሎች ምክንያቶች ቁልፍ ግኝቶችን ያጠቃልላል።

ለቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ መጤዎች ዲጂታል ማካተት ተደራሽነት እና ብቃቶች 2 ዋና መሰናክሎች ናቸው።

ለዚህ ቡድን ዲጂታል ማካተት ሌሎች እንቅፋቶችን የሚፈጥሩ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ዝቅተኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት
- ባህላዊ መሰናክሎች
- ዝቅተኛ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ።

## 2.1. የስነ-ጽሁፍ ግምገማ ማጠቃለያ

በኒው ዚላንድ ውስጥ እና ሌሎች የዓለም ሀገራት ዙሪያ እንግሊዝኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ (ESL) ነባር ስደተኞች እና መጤዎች በዲጂታል ማካተት ላይ ለነባር ስነ-ጽሁፍ አምስት የውሂብ ቋቶች ተፈልገዋል። በረቂቆች ላይ የመጀመሪያ ማጣራት 36 መዝገቦችን አፍርቷል። ከዚያ፣ እያንዳንዱ መዝገብ ከጥናቱ ወሰን ጋር ያለውን ጠቀሜታ ለማወቅ ተገምግሟል።

እንዲሁም ግንዛቤዎቹ የጥናቱን እቅድ ለማሳወቅም ጥቅም ላይ ውለው ነበር።

### በ ‘ስደተኞች’ እና ‘መጤዎች’ መካከል ያሉት የትርጉም እና ተሞክሮ ልዩነቶች

በስደተኞች እና መጤዎች መካከል ግልጽ የሆኑ የህግ ልዩነቶች አሉ፣ እነዚህም በኒው ዮርክ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች እና መጤዎች ጠቅላላ ጉባኤ መግለጫ (UN ጠቅላላ ጉባኤ፣ 2016) እና በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

ስደተኞች እና መጤዎች ወደ አዲስ ሀገር በሚደርሱበት ጊዜ በተለየዩ ተሞክሮዎች ውስጥ ያልፋሉ። በኒው ዚላንድ፣ እነዚህ ቡድኖች በኒው ዚላንድ ኢሚግሬሽን (INZ) ከሌሎች መንግስታዊ ወኪሎች ጋር አንድላይ በመሆን እና በሶስተኛ ወገን አቅራቢዎች የተለያየ የሰፈራ ድጋፎችን ይቀበላሉ።

### በ ‘ስደተኞች’ እና ‘የተገለሉ መጤዎች’ መካከል ያሉ ተገማች ተመሳሳይነቶች

በሰፈራ ጉዟቸው ወቅት የቀድሞ ስደተኞች የተጋፈጡዋቸውን ችግሮች የተጋፈጡ የመጤ ቡድኖች ይኖራሉ። እነዚህ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን ያካትታሉ። ይህ ቡድን በ ቢሎንግ ኦቴሮዋ እና ሌሎች በኒው ዚላንድ ውስጥ ያሉ NGO ዎች ‘የተገለሉ መጤዎች’ በመባል ይገለፃል። (ቢሎንግ ኦቴሮዋ፣ UMMA ትረስት፣ RASNZ፣ የኒው ዚላንድ ቀይ መስቀል፣ የጥገኝነት ፈላጊዎች ትረስት፣ ኦቴሮዋ ድጋሚ ሰፋሪ ህብረተሰብ ጥምረቶች፣ ቤተሰብ ተግባር፣ 2020)።

በማጠቃለያ፣ በቀድሞ ስደተኞች እና የሰፈራ አገልግሎቶች ተደራሽነት የሚያስፈልጋቸው የተገለሉ መጤዎች መካከል ከፍተኛ ደረጃ ያለው ተመሳሳይነት አለ። በቀድሞ ስደተኞች እና እንደ ባለሙያ መጤዎች ባሉ ሌሎች የመጤ ቡድኖች መካከል ዝቅተኛ መመሳሰል አለ። በዚህ ጥናት ውስጥ፣ የቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ መጤዎች ዋና ትኩረቶች ናቸው።

### ከስነ-ስሁፍ ግምገማው የተለዩ ቁልፍ ጭብጦች

- በቅርብ ጊዜ በመጡ ስደተኞች እና መጤዎች ላይ ከይፋዊ ምንጮች በመስመር ላይ መረጃን መጠቀም ላይ መሰናክሎች አሉ።
- ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ስደተኞች እና መጤዎች ከቁልፍ ፍላጎቶቻቸው አንዱ የሆነውን፦ በማህበራዊ መለያዎቻቸው አማካኝነት ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መገናኛን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ሆኖም፣ ዲጂታል መሳሪያዎችን ለእነሱ ጥቅም በማዋል ረገድ መሰናክሎች አሁንም አሉ።
- በዲጂታላዊ የተካተቱ ሰዎች የተሻለ ማህበራዊ መካተት እና ደህንነትን ያሳካሉ።

በስነ-ስሁፍ ግምገማው እንደተመለከተው፣ እነዚህ 3 ቁልፍ ጭብጦች በ ዲጂታል ማካተት ምርምር አጀንዳ ውስጥ እንዲሁም የዚህን ጥናት ወሰን ለማሳወቅ ጥያቄዎችን በከፊል ለመመለስ ይረዳሉ።

ለቀድሞ ስደተኞች እና መጤዎች በዲጂታል ማካተት ላይ ያሉ መሰናክሎች በአዲስ ተቀባይ ሀገራቸው ሲሰፍሩ የሚፈጠሩ ችግሮች እንደ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ያሉ ችግሮች ከሌሎች ምክንያቶች ጋር ይዋሃዳሉ።

የዲጂታል ማካተት ባህሪዎችን ማሻሻል — ማነሳሳት፣ ተደራሽነት፣ ብቃቶች እና ተዓማኒነት (MAST) — የቡድኑን ዲጂታል ማካተት እንዲሁም ከሰፈራ ጉዟቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን ያሻሽላል ተብሎ ይገመታል።

## 2.2. የጥናት ግኝቶች ማጠቃለያ

የጥናት ግኝቶቹ ከ MAST ማዕቀፍ በተቃራኒ ተገምግመዋል፣ ይህም የሚከተሉትን 4 እርስ በርሳቸው የተደጋገፉ ባህሪያት ያጠቃልላል፦ ተነሳሽነት፣ ተደራሽነት፣ ብቃት እና እምነት።

### ተነሳሽነት

አንዳንድ የቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ መጤዎች ወደ ኒው ዚላንድ ከመምጣታቸው በፊት የዲጂታል መሳሪያዎችን፣ በይነ መረብን ወይም የመስመር ላይ አገልግሎቶችን በተመለከተ ምንም የቀደመ ተሞክሮ የላቸውም። ይህ በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ምን ማሳካት እንደሚቻል በእውቀታቸው ላይ ክፍተትን ይፈጥራል።

የፍላጎቶች ተዋረድ ቅድሚያ ይሰጠዋል፣ እናም የመማር አእምሮአዊ ዝግጁነት በጣም አናሳ ነው። ለእነዚያ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ለተረዱ፣ በጠቃሚ መሳሪያዎች እና ብቃቶች እጥረት ምክንያት እነዚህ ጥቅሞች አይስተዋሉም። ለዚህ ቡድን በውጭ ሀገር ካሉ ቤተሰቦች እና ጓደኞች ጋር መገናኘት ትልቁ ተነሳሽነት እና በስማርት ስልኮች በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

> “እጅግ ረጅም ጊዜ ፈጅቶብኛል፣ ምንም እንኳን አብሬያቸው እንደተማርኳቸው ልጆች ወይም ጓደኞች ስማርት ስልኮችን አግኝተው ብቅ ማለት ጀመሩ። እኔ ወድያውኑ ስማርት ስልክ አልነበረኝም ነበር። እንደገና ግን፣ ያ ራሱ ፈተና አልመሰለኝም ነበር፣ ምክንያቱም ስማርት ስልክ ምን ማድረግ እንድሚችል አላውቅም ነበረ። እናም ስልኬ እስኪሰበር ድረስ ኑሮዬን ተላምጄው ነበረ። ከዚያም አዲስ ማግኘት ነበረብኝ። እና በስተመጨረሻ ለእኔ እና ለእናቴ ስማርት ስልክ አገኘን። 3 ዓመታትን ወሰደብኝ።”
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ

## ተደራሽነት

ወጪ ለዚህ ቡድን እንደ ዴስክቶፕ፣ ላፕቶፕ፣ ተንቀሳቃሽ ውሂብ እና እቅዶች፣ እንዲሁም ገደብ የለሽ የቤት በይነ መረብ ያሉ የበለጡ መሳሪያዎችን እንዳያገኙ ዋናው መሰናክል ነው። ከነፃ የህዝብ ዋይፋይ ጋር የሚኖር ግንኙነት፣ በዝቅተኛ ፍጥነት ወይም የጊዜ-ገደብ፣ ወይም በሁሉም የተነሳ ቀጣይነት ያለው እንዳልሆነ ተመልክቷል።

የመንግስት አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ በአካል መጎብኘት ጠቃሚ ነገሮችን ለማካሄድ እና ጉዳዮችን እና ጥያቄዎችን ለመፍታትት አሁንም የበለጠ ውጤታማው መንገድ ተደርጎ ይታያል።

በመጀመሪያዎቹ 3 ወራት፣ ከትርጉም አገልግሎት ጋር በአካል የሚደረጉ ወይም በስልክ የሚደረጉ ቀጠሮዎች ተመራጭ የሆኑ አገልግሎት ማግኛ መንገዶች ናቸው። እንደ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ፣ የሰፈራ ሰራተኞች፣ የቤተሰብ አባላት ወይም የማህበረሰብ አባላት ያሉ የማህበራዊ አውታረ መረቦች ድጋፍ ለዚህ ቡድን በይነ መረብ፣ መሳሪያዎች እና የመስመር ላይም ሆኑ የመስመር ውጭ ጠቃሚ አገልግሎቶች ተደራሽነት ቁልፍ ናቸው።

የግል-አገልግሎት የመስመር ላይ ተደራሽነት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ገደብ፣ በብሄረሰብ ቋንቋ ያሉ መገልገያዎች እጥረት፣ የተገደቡ ዲጂታል ክህሎቶች፣ እና የመስመር ላይ ስርዓቶች እንዴት እንደሚሰሩ ባለማወቅ ምክንያት አይቻልም። ይህ ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ ለብዙዎቹ እነዚህ ቡድኖች በኒውዚላንድ ከሰፈሩ ለመጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት ሳይቀየር የሚቆይ ይሆናል።

ለእነዚያ የመስመር ላይ የግል-አገልግሎቶችን ለመጠቀም ፈቃደኝነት ላላቸው፣ ጊዜ ወሳጅ ነው ምክንያቱም ይዘቱን እና መተግበሪያውን ለመረዳት እንዲያግዛቸው የመስመር ላይ መተርጎምያ መሳሪያዎችን መጠቀም አለባቸው። እነዚያ ጥረቶች ቢኖሩም፣ ለጥያቄዎች፣ መስፈርቶች እና ቴክኒካዊ ቃላቶች እርዳታ አሁንም አስፈላጊ ነው።

> “ከመምጣታችን በፊት ስለ ኒውዚላንድ ምንም ነገር አናውቅም ነበር። በመሠረቱ፣ ወደ ኒውዚላንድ ከመምጣታችን በፊት፣ ስለ ኒውዚላንድ ትንሽ መረጃ ተሰጥቶን ነበር። እውነቱን ለመናገር፣ ኒውዚላንድ የት እንድሆነ ራሱ አናውቅም ነበር። ወደ እዚህ መልሶ ማቋቋሚያው ወኪል ስደርስ፣ [a] የበጎ አድራጎት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ አቀረቡልኝ፣ እሷ ሁሉንም ነገር በሚባል ደረጃ አደረገችልኝ፣ እንደ እንዴት ገበያ መሄድ እንዳለብኝ፣ የባንክ ካርድን እንዴት መጠቀም እንደምችል፣ እንዴት መሥራት እና ገቢ ማግኘት እንዳለብኝ፣ ወይም እንዴት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እንዳለብኝ፣ እንዴት \ አውቶቡስን መጠቀም እንዳለብኝ ወይም በአዲስ ማህበረሰብ ውስጥ እንድሰፍር በሁሉም ነገር ላይ ይህቺ የእርዳታ ሰራተኛ ረዳችኝ እና መራችኝ እና መከረችኝ እንዲሁም ደገፈችኝ።”
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ

## ክህሎቶች

በብሄረሰብ ቋንቋ የሚቀርብ የዲጂታል ብቃቶች ስልጠና ያለ እንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት የዲጂታል ብቃቶችን የማግኛ ሂደት የሚያመቻች መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች አሉ። ሆኖም፣ ስልጠናው ውጤታማ እንዲሆን፣ በዲጂታል ብቃት ደረጃ ግልጽ የሆነ ልዩነት መኖር አለበት። የታመኑ ማህበረሰቦች እውቀትን ለማስተላለፍ፣ ድጋፍ ለመስጠት፣ እና የዲጂታል ብቃቶች ስልጠናዎችን ለማመቻቸት እንደ መካከለኛ በተሻለ ሁኔታ ተቀምጠዋል።

ለዚህ ቡድን 3 ቱ ዋና ዋና እጅግ አስፈላጊ አካባቢዎች የዲጂታል ብቃቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የመስመር ላይ ግብይት ብቃቶች
2. የመስመር ላይ ደህንነት እና ጥበቃ ብቃቶች
3. የመስመር ላይ መራጃዎችን እና ይዘቶችን የመያዝ ብቃቶች ናቸው።

ለዚህ ቡድን ማሻሻል የሚፈልጉዋቸው 5 ቱ ዋና ዋና ልዩ የዲጂታል ብቃቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በደመና ላይ መረጃን ማስቀመጥ እና ከተለያዩ መሳሪያዎች ያንን ይዘት መጠቀም
2. ቫይረሶችን እና ሌሎች አደጋዎችን ለመከላከል መሳሪያዎችን በየጊዜው ማደስ
3. ገንዘባቸውን እና ግብይቶቻቸውን በመስመር ላይ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ማስተዳደር
4. የህዝብ አገልግሎቶችን በመስመር ላይ ማግኘት እና መጠቀም፣ ለምሳሌ፣ መኪና ምዝገባ፣ MyMSD
5. ለእቃዎች ወይም አገልግሎቶች ክፍያ በመስመር ላይ መፈጸም።

አብዛኛው ስልጠናዎች በእንግሊዝኛ የሚሰጡ ስለሆኑ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ማነስ የዲጂታል ክህሎቶችን ለማግኘት ትልቅ እንቅፋት ነው።

> “ነጻ ክፍለ ጊዜ ለአዋቂዎች በጣም ጠቃሚ ነው ምክንያቱም ለአዋቂዎች ማለቴ፣ ኮምፒውተር ቢኖረንም፣ ብዙ ሰዎ \ ሊከፍቱት አይችሉም፣ እንዴት እንደሚጠቀሙበት አያውቁም፣ ስለዚህ እንደዚ አይነት የኮምፒውተር ትምህርት ለእነሱ በጣም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ሁለተኛው ችግሩ ይህ ትምህርት በእንግሊዝኛ መሰጠቱ ነው። ሌላ ትልቅ ችግር አለ። ስለዚህ በእኛ ቋንቋ የሚያስተምር የሆነ ሰው ቢኖር፣ ይሄ በጣም የተመሰገነ ነበር። ምክንያቱም አሁን፣ ቴክኖሎጂ ሁሉም ቦታ አለ። ስለዚህ በዚህ ጊዜ፣ ሁሉም ሰው ቢያንስ መሰረታዊውን ትምህርት መረዳት አለበት። እና እኛ እንዳልነው፣ መንግስት ወይም ብዙ ተቋማት እነዚህን ነጻ ትምህርቶች ይሰጣሉ፣ ነገር ግን አሁንም ለኛ በጣም ከባድ ነው። ምክንያቱም እኛ አናውቅም፣ ብዙ ሰዎች እንግሊዝኛ አያውቁም። የኮምፒውተር ቃላቶች ለመረዳት የበለጠ ከባድ ናቸው።”
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ

ዝቅተኛ በራስ-መተማመን እና የኑሮ መሰረታዊ ፍላጎቶችን የማሟላት ቀደሜታ የሚደረጉ የስልጠና ክፍለ ጊዜዎች መገኘት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

በዚህ ቡድን ውስጥ ሴቶች በዝቅተኛ የዲጂታል ብቃቶች እና ዕድሎችን የማግኘት እና በዋነኛነት ከህመም እና ጉዳቶች ጋር በሚከተሉ፣ የቤት ውስጥ እንክብካቤ የመስጠት ግዴታዎች ምክንያት፣ የስልጠና ክፍለ ጊዜዎች ላይ እንዲገኙ ድጋፍ እጥረት ምክንያት በዲጂታል ያለመካተት የበለጠ ስጋት አለባቸው።

## እምነት

የግላዊ መረጃዎች ፍርሃት — የብድር ካርድ እና የባንክ ዝርዝሮችን ጨምሮ — ክትትል መደረግ፣ መጠመድ እና ተዛማጅነት ለሌላቸው ዓላማዎች መሰብሰብ የእምነት መጉደል ዋነኛው ምንጭ ነው። ይህ ቁልፍ ለሆኑ አገልግሎቶች እንደ የመስመር ላይ ግዢ፣ የመስመር ላይ ባንክ አገልግሎት እና የመስመር ላይ ክፍያዎች ያሉ የመስመር ላይ ተግባራትን ለማድረግ መሰናክሎችን ይፈጥራል።

> “እኔ የማልወደው እጅግ አሳሳቢው እና እጅግ የማይታመነው ነገር የማንነት ስርቆት ነው እና እንደምታውቁት፣ ለመረጃችሁ፣ ጠንቃቃ ሁኑ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እንደሚወስዱት እና ያንን ቅጽ ስትሞሉ ትክክለኛውን ነገር እንዳደረጋችሁ ማወቅ አትችሉም።”
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ

እንደ የመስመር ላይ ያሉ ማታለሎች፣ ማጭበርበሮች እና ጠለፋዎች ያሉ የሳይበር ወንጀሎች ከዚህ ቀደም- ወይም ሁለተኛ- ተሞክሮዎች እንዲሁ በዲጂታል አለም ላይ ያለውን አመኔታ ቀንሰውታል።

እጅግ አመኔታ ያላቸው ማህበራዊ አውታረ መረቦች፣ በመንግስታት ክትትል የሚደረግባቸው ድረ ገጾች፣ ጣብያዎች እና የታወቁ የባንክ ብራንዶች፣ የቴሌ ግንኙነቶች እና የዜና ማሰራጫዎች ናቸው። ማህበራዊ ተጽዕኖም እንዲሁ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን አቀባበል የሚያመቻች አስፈላጊ ምክንያት ነው።

## 2.3. የዚህ ቡድን ዲጂታል ማካተት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ምክንያቶች

በዲጂታል ማካተት ማዕቀፍ ውስጥ ከ 4 ቱ ባህሪያት በተጨማሪ፣ የዚህ ቡድን ዲጂታል ማካተት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ምክንያቶች አሉ።

### የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቁነት እና የአገልግሎት መገኘት ግንዛቤ ማነስ

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት እና በብሄረሰብ ቋንቋ ያሉ መገልገያዎች ማነስ ለዚህ ቡድን ዲጂታል ማካተት የረጅም-ጊዜ መሰናክሎች ናቸው።

ይህ በተለይ ለእነዚያ በመንግስት መልሶ ማቋቋም መርሃ ግብሮች ለመቀጠል ብቁ ላልሆኑ ሰዎች፣ በኒውዚላንድ ውስጥ ነገሮች እንዴት እንደሚሠሩ፣ እና ምን የመንግስት መረጃ እና አገልግሎቶች እንደሚገኙ፣ ካለማወቅ ወይም ካለመረዳት የተነሳ ተባብሷል።

> "ማለቴ፣ አሁን ላይ ካለው ቴክኖሎጂ ጋር ሲነጻጸር፣ ሁሉም ነገር ከባድ ነበር። ነገርግን ያኔ፣ ቁልፍ አገልግሎቶቹ ምን እንደሆኑ ሙሉ በሙሉ አልውቅም ነበር፣ በዚያን ጊዜ ምን እንዳልነበረህ ሙሉ በሙሉ ባለማወቅህ ምክንያት፣ ስለዚህ በቃ ባለህ ነገር እንደ ማድረግ ታደርገዋለህ እና 'ይሄ ከባድ ነው እንዴ' ብለህ እንኳን አታስብም፣ ዝም ብለህ ታደርገዋለህ።"
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ

### ባህላዊ መሰናክሎች

ስለ ግንዛቤ ስታነሳ ወይም ስለ የመንግስት አገልግሎቶችን ማቅረብ፣ ወይም ሁለቱን ስለ መስራት — በተለይ በመስመር ላይ ከሆነ ባህላዊ መገለጫዎች ከግምት ውስጥ መግባት ያስፈልጋቸዋል። አንዳንድ ባህሎች ጥያቄዎችን ወይም እርዳታን መጠየቅ አሳፋሪ ነው ብለው ይቆጥራሉ። አንዳንድ ሰዎች ሌሎች ሰዎች ጋር አስቸጋሪ ሆነው መገኘት አይፈልጉም። ይህ በተለይም አገልግሎቶቹ በመስመር ላይም ሆነ ከመስመር ውጪ በተገቢው-መልኩ የማይደርሱ ከሆነ፣ ለአገልግሎት አቅራቢዎቹ የአስተያየት እጥረትን ያስከትላል — ለምሳሌ፣ በስልክ ወይም በአገልግሎት ማዕከል ላይ።

> "እንደ ለእርዳታ ጥያቄዎችን መጠየቅ ወይም እንደዛ አይነት ነገር ... ምክንያቱም ባህሉ መጠየቅ ትንሽ የሚያሳፍር አይነት ስለሆነ፦ ሊረዱኝ ይችላሉ? \በቅድመ እይታ በእርግጠኝነት አደርገዋለሁ፣ የማይገባኝ ቢሆንም እንኳን እጠይቃለሁ።"
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ

### የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ

ዝቅተኛ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ለዚህ ቡድን ዲጂታል ማካተት ላይ፣ በተለይም በዲጂታል መሳሪያዎች፣ የተንቀሳቃሽ ውሂብ እና እቅዶች፣ እና ገደብ የለሽ የቤት በይነ መረብ ተደራሽነት ላይ ተጨማሪ መሰናክል ይፈጥራል። የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃን ለማሻሻል ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ምክንያት ይህ በ MAST ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ የተነሳሽነት፣ ተደራሽነት፣ እና ብቃቶች ባህሪይ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

### ትምህርት ማግኘት

ከፍተኛ ትምህርት ማግኘት በተለይ ከብቃት ባህሪይ ጋር በተያያዘ ከከፍተኛ ደረጃ የዲጂታል ማካተት ጋር ግንኙነት ያለው ይመስላል። ይህ በኒውዚላንድ ከፍተኛ ትምህርት በተከታተሉ ወይም በመከታተል ላይ ባሉ የቀድሞ ስደተኞች እና የከፍተኛ ትምህርት ዳራ ባላቸው በአንዳንድ መጤዎች ላይ ታይቷል።

## 2.4. ዲጂታል ማካተት እና ደህንነት

### የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት

ዲጂታል ማካተት በተለይም ወደ መስመር ላይ የራስ-አገልግሎቶች ጋር ከሚደረገው ሽግግር ጋር በተያያዘ፣ የዚህ ቡድን የረጅም ጊዜ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ላይ በከፊል ተጽዕኖ ያሳድራል። ለዚህ ቡድን፣ በማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት እና በሀገራቸው እና በኒውዚላንድ መካከል ያሉት የመዳረሻ ዘዴዎች ልዩነት ይንጸባረቃል። ይህ ለአብዛኞች የቀድሞ ስደተኞች እና መጤዎች የቀደመ የበይነ መረብ እና ዲጂታል መሳሪያዎች የመጠቀም ልምድ ማጣት፣ እንዲሁም በአነስተኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ይባባሳል። ይህ የመስመር ላይ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ፈታኝ ያደርገዋል።

በኒውዚላንድ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ 3 ወራት፣ የበጎ ፍቃደኞች፣ ሰፈራ ሰራተኞች፣ ቤተሰቦች፣ ጓደኞች እና የማህበረሰብ አባላት ድጋፍ ለአስፈላጊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ቁልፍ ነው። ተመራጭ የመዳረሻ ዘዴዎች በአካል የመገናኘት ቀጠሮዎች እና የስልክ ጥሪዎች ናቸው። ይህ ሁኔታ ላለፉት 3 ዓመታት ሳይቀየር ቆይቷል።

### ማህበራዊ ግንኙነት እና ግለሰባዊ ደህንነት

በኒውዚላንድ ውስጥ የስማርት ስልኮች ዋጋ ተመጣጣኝነት፣ ከአንፃራዊ ቋሚ በይነ መረብ ጋር የተደገፈ፣ እንደ የቤት ውስጥ ዋይፋይ፣ ለዚህ ቡድን ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚገናኙበትን ኢኮኖሚያዊ እና ቋሚ የሆነ መንገድን ይፈጥራል። ስለዚህ፣ ዲጂታል ማካተት ለዚህ ቡድን ያለሱ ሊሆኑ የማይችሉትን የባህር ተሻጋሪ የቤተሰብ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን እንዲጠብቅ ያስችላል። ይህ በተለይ አዲስ በመጡት ላይ፣ የብቸኝነት እና መገለልን ስሜት በመቀነስ በቀጥታ ደህንነታቸው ላይ ጠቀሜታ አለው።

የበይነ መረብ ግንኙነቶች በሚቋረጥበት ወቅት፣ እኚህ ቡድኖች ከባህር ማዶ ቤተሰቦቻቸው ሁኔታ ጋር ግንኙነት በሚያቋርጡበት ጊዜ በግለሰባዊ ደህንነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። በኒውዚላንድ ውስጥ መቋረጥ በውሂብ ጣሪያ መድረስ ወይም በይነ መረብ መቆራረጥ ሊሆን ይችላል። በመጀመሪያ ሀገራቸው፣ የአውታረ መረብ መሰረተ ልማት ወይም ግንኙነት የሚቋረጠው በማህበረ-ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ወይም ከፍተኛ የበይነ መረብ ዋጋ ሊሆን ይችላል።

> “ወላጆቼ፣ ወንድሜ እና 2 እህቶቼ ሀገርቤት አሉ። እንዳለመታደል ሆኖ፣ በዚያ አካባቢ ላይ የቀጠለ ጦርነት በመኖሩ ምክንያት በጥሩ ሁኔታ ላይ አይደለም ያሉት። ስለ እሱ ማሰብ አስጨናቂ ነው። አውታረ መረቡ ስለሚቆራረጥ በጣም ከባድ ነው። ስለዚህ በቀጥታ ዝም ብዬ ልደውልላቸው። መደበኛ አገልግሎቶች ስለማይሰሩ እና ስለማያገናኙኝ፣ ወደ እነሱ ለመደወል የተለየ መተግበሪያ እጠቀማለሁ። አዎ፣ ስለዚህ አሁን መተግበሪያውን ጭኜዋለሁ። ቻርጅ እናድርገው እና ያ የሚሰራልን ከሆነ በቀጥታ እንደውልላቸው። እናም በአሁኑ ጊዜ እየሰራ አይደለም።”
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ



# ३. ማጠቃለያ እና ምክሮች

ለዚህ ቡድን አብዛኛዎች፣ በዲጂታል ማካተታቸው ላይ የመጀመሪያዎቹን 3 ወራት ከመጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት የሰፈራ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ብዙም ለውጥ የለውም። ሆኖም፣ ለረጅም ጊዜ በኒውዚላንድ ለሚሰፍሩ — ለምሳሌ፣ ከ 10 ዓመታት በላይ፣ የዲጂታል ማካተት የመሻሻል ስሜት አለ።

ይህም የተደራሽነት እና ብቃት ባህርያትን በመጀመሪያዎቹ የሰፈራ ጉዟቸው በመተግበር ለዚህ ቡድን ዲጂታል ማካተት ጉዞ የማፋጠን እድልን ይፈጥራል።

እንደ በጎ ፍቃደኞች፣ ሰፈራ ሰራተኞች፣ ማህበረሰባት እና የቤተሰብ አባላት ያሉ ማህበራዊ አውታረ መረቦች፣ በይፋዊ የመንግስት ጣቢያዎች እና ድረገጾች ተከትለው፣ እጅግ ተዓማኒነት ያላቸው ምንጮች ናቸው። ስለዚህ፣ እነዚህ አውታረ መረቦች የበለጠ ጥቅም ላይ ሊውሉ፣ እንዲሁም ጣቢያዎች እና ድረገጾች የዚህን ቡድን ዲጂታል ማካተት እንዲያሻሽሉ አካታች በሆነ መልኩ ሊነደፉ ይገባቸዋል።

ከታች የሚገኙት ምክሮች በጥናታዊ ግኝቶች ላይ የተመሰረቱ እንጂ፣ በመንግስት ፖሊሲ ላይ የተመሰረቱ አይደሉም።

## የተደራሽነት ጉዳዮችን መቅረፊያ እድሎች

የተደራሽነት ጉዳዮችን ለመቅረፍ፣ የሚረዱ እርምጃዎች የሚከተሉትን ማቅረብ ያካትታል፡-

- በተለየዩ የገንዘብ አማራጮች እንደ ላፕቶፖች ያሉ መሳሪያዎች እና የበይነመረብ ግንኙነቶች ውጤታማ አቀራረብ እንደሆነ ተገምግሟል። የትምህርት ሚኒስቴር እኩል የሆነ የዲጂታል ተደራሽነት መርሃ ግብር የተሳካ አቀራረብ ምሳሌ ነው
- አስፈላጊ የሆኑ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ጨምሮ ቁልፍ የመስመር ላይ አገልግሎቶችን ለማግኘት ባዶ-ደረጃ ያለው ውሂብ
- የዲጂታል ብቃቶች ስልጠና እና የመሳሪያ ጣቢያዎች ተደራሽነት ያላቸው እንደ የህዝብ ቤተ-መጽሃፍት ያሉ የማህበረሰብ ቦታዎች እና የአምልኮ ቦታዎች።

## የብቃት ጉዳዮችን የመቅረፍ እድሎች

የብቃት ጉዳዮችን ለመቅረፍ ለማገዝ፣ የሚረዱ እርምጃዎች የሚከተሉትን ማቅረብ ያካትታል፡-

- ይህ ቡድን በዲጂታላዊ ሳይካተት የሚቆይበትን ጊዜ ለመቀነስ ተዓማኒነት ባላቸው አማካይነት በብሄረሰብ ቋንቋዎች የዲጂታል ብቃቶች ስልጠና
- በብሄር ማህበረሰቦች ውስጥ ላሉ ሴቶች በተለይም በቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጭ ተግባራት ዙሪያ የስልጠና ክፍሎች እንዲካፈሉ የታለመ እና ሁለንተናዊ ድጋፍ
- የዲጂታል ብቃቶች ስልጠና ሃያል እና ውጤት እንዲኖረው ግልጥ የስኬት ደረጃዎችን ለምሳሌ፣ በስማርትፎን ላይ የተመሰረተ የዲጂታል ክህሎት ስልጠና እንደመነሻ ሆኖ ወደ እንደ ላፕቶፕ ውስብስብ የዲጂታል ብቃቶች ስልጠና ተለቅ ባሉ መሳሪያዎች ላይ

- ለዚህ ቡድን አስፈላጊ ተብለው በታወቁት ከፍተኛዎቹ 3 የዲጂታል ብቃት መስኮች፡ የመስመር ላይ ግብይት ክህሎቶች፣ የመስመር ላይ ደህንነት እና ደህንነት ችሎታዎች፣ እና የመስመር ላይ መረጃን እና ይዘትን የመቆጣጠር ችሎታዎች ላይ ያተኮረ ስልጠና ነው። ይህ ቁልፍ የመስመር ላይ አገልግሎቶችን ስለማግኘት እንደ MyMSD፣ myIR፣ የመስመር ላይ የስደተኞች መለያ እና የመስመር ላይ ባንክ ያሉ ስልጠናን ያካተተ መሆን አለበት።

# ሌሎች ታሳቢዎች

በኒውዚላንድ ውስጥ የሚኖሩ የቀድሞ እና የተገለሉ ስደተኞችን በዲጂታል ለማካተት፣ የሚከተለውን ያስቡበት፡-

- የእንግሊዘኛ ቋንቋ የብቃት ስልጠና ቅድሚያ መስጠትን መቀጠል
- በብሄር ቋንቋዎች በመስመር ላይ በተለይም ለቁልፍ አገልግሎቶች መገልገያዎች እንዲገኙ ማድረግ
- ለቀድሞ ስደተኞች እና የተገለሉ ስደተኞች መልሶ የማቋቋሚያ ፕሮግራም የዲጂታል ማካተት ስልጠና አካል ማድረግ በESL
- ለመጀመሪያዎቹ 3 እና 5 የስምምነት ዓመታት የዲጂታል ማካተት ድጋፍን ለመጨመር ተጨማሪ ኢንቨስትመንት
- የጥንት ዲጂታል ማካተት ድጋፍ በሰፈራ ውጤቶች ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመረዳት የረጅም ጊዜ ጥናቶችን በመጠቀም
- በ ኒውዚላንድ ውስጥ በሰፈራ እና በሰፈራ ውጤታቸው ውስጥ የዚህን ቡድን ዲጂታል ማካተት አቀማመጥ መለካት እና መከታተል።

> “ከባህር ማዶ እየመጣሁ ነው፣ እንግሊዘኛ አስተምሩኝ፣ ቋንቋውንም ተምሬያለሁ፣ እና እዚህ እሰራለሁ፣ ግብር እከፍላለሁ፣ መንግስትን እረዳለሁ። ስለዚህ የማልጠቅም አልሆንም፣ ጠቃሚ ግን እሆናለሁ።
>
> ሂሳብ እና እንግሊዘኛ ስታስተምሩኝ፣ ይበልጡን ጠቃሚ እሆናለሁ። ከመቼውም የበለጠ ትልቅ ነገርን አደርጋለሁ።
>
> ኮምፒዩተር ስታስተምሩኝ፣ የ IT፣ እንግሊዘኛ እና ሒሳብ መሰረት ይኖረኛል። ወደፊትም ባለሙያ እሆናለሁ እናም ኒውዚላንድ በፍጥነት እና በፍጥነት እንድታድግ እረዳለሁ።”
>
> — የጥናቱ ተሳታፊ



# 4. ማጣቀሻዎች


Belong Aotearoa, UMMA Trust, RASNZ, NZ Red Cross, Asylum Seekers Support Trust, Aotearoa Resettled Community Coalition, and Family Action. (2020). 'Understanding social work provision to former refugees and marginalised migrant communities in Auckland.' (PDF, 1.650 MB). https://static1.squarespace.com/static/5cca54599e483d0001fff53b/t/5f10c712d863ea7a41fc368a/1594935071412/Social+Work+Research+Report+FINAL_2020.pdf

Department of Internal Affairs. (ሜይ፣2019). 'Digital inclusion stocktake: What digital inclusion looks like across government.' https://www.digital.govt.nz/dmsdocument/155-digital-inclusion-stocktake-what-digital-inclusion-looks-like-across-government/html#executive-summary

Digital Inclusion Research Group. (ሜይ፣2017). 'Digital New Zealanders: The Pulse of our Nation.' MBIE and DIA. https://www.mbie.govt.nz/dmsdocument/3228-digital-new-zealanders-the-pulse-of-our-nation-pdf

UN General Assembly. (ኦክቶበር 3፣ 2016). 'New York Declaration for Refugees and Migrants: resolution / adopted by the General Assembly.' Refworld. https://www.refworld.org/docid/57ceb74a4.html

UNHCR. (ኦገስት 31፣ 2018). ''Refugees' and 'Migrants'— Frequently Asked Questions (FAQs).' Refworld. https://www.refworld.org/docid/56e81c0d4.html




digital.govt.nz